# የሥራ ሜኑ

"ምን ልሥራ?" ለሚሉ

## 1000+ ሥራዎች



በሐገራችንና በውጪ ሐገራት
እየተሰሩ ያሉትንና
አዳዲስ የሥራ ዓይነቶችን ዝርዝር የያዘ!

በቅድስት ባዩ

# የሥራ ሜኑ

## “ምን ልስራ?” ለሚሉ

## 1000+ ሥራዎች

አዘጋጅ፡ ቅድስት ባየ

2013ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!

All Rights Reserved!

© ቅድስት ባዬ

ያለ አዘጋጁ ፈቃድ ኮፒ አድርጎ ለግል ጥቅም ማዋል፣ በከፊልም ሆነ በሙሉ መልሶ ማሳተም በህግ ያስቀጣል።

No part of this publication can be copied or duplicated in any way.

የመጀመሪያ ዕትም፡ መጋቢት 2013 ዓ.ም

አሳታሚና አከፋፋይ፡

ኦክስፎርድ ኢንስቲትዩት እና ሁለገብ የማስታወቂያና

የሥራ ፈጠራ ማዕከል

0911 60 65 05

Telegram: HULEGEB TUBE ETH

**ለአስተያየትዎ**

09 93-51 35 95 (Telegram, Text message)

E-mail: kidistbaye3@gmail.com

# ም ስ ጋ ና

ይህን መጸሐፍ ሳዘጋጅ ሙያዊ እገዛ በማድረግ ለረዳኸኝ የብዙ ፊጠራዎች ባለቤት - ኢንተርፕረነርና የቢዝነስ አማካሪ አቶ ነጋሲ አርአያ እንዲሁም ዶ/ር ወሰን ተስፋየ እና አቶ ኃይለማርያም ባየ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በተጨማሪም የበኩላችሁን ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ እና ስፖንሰር የሆናችሁ ድርጅቶችን ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡

# ማ ው ጫ

**ይዘት** **ገጽ**


- መግቢያ........................................ 1
- ሥራ የምንመርጥባቸው መንገዶች........................ 6
- የንግድ አጀማመር ሂደት........................ 21
- የሥራ ዘርፎች........................................ 22
- 1000+ የስራ ዝርዝሮች........................ 23
- የገበያ ጥናት (ምሳሌ) ........................ 94
- ቢዝነስ ፕላን (ምሳሌ) ........................ 98
- ራዕይ፣ተልዕኮና ግብን ማወቅ........................ 115
- የንግድ ስም እንዴት እንምረጥ........................ 121
- የንግድ ማስታወቂያ........................ 124
- ደንበኛ አያያዝ........................ 130
- ተፎካካሪዎችን የማሸነፍ ጥበብ........................ 135
- ምርትንና አገልግሎትን ማሳደግ........................ 143
- መሰናክሎችን እንዴት እንለፍ........................ 153
- መሰረታዊ የጊዜ አጠቃቀም........................ 164
- መሰረታዊ የገንዘብ አጠቃቀምና ቁጠባ........................ 168
- የቢዝነስ መጻሐፍት ጥቆማ........................ 177
  እና ዋቢ መጻሐፍት

# መ ግ ቢ ያ

አብዛኞቻችን አዲስ የንግድ ስራ ለመጀመር ስናስብ "ምን አይነት ስራ ብጀምር ይሻላል?" በሚል ብዙ እንጨነቃለን፡፡ በአብዛኛው የተለመዱና በአካባቢያችን የምናያቸው ጥቂት የስራ አይነቶች ብቻ ወደ አዕምሯችን ስለሚመጡ ከእነዚህ ስራዎች ውጭ ሌላ አማራጭ ባለማስተዋል "በቃ ይህን ልስራ ሌላ ምን ልሰራ እችላለሁ?" በማለት አንዱን ስራ ልንጀምር እንችላለን፡፡ ይህ በተለይ በጥቃቅንና አነስተኛ ስራዎች ላይ በስፋት ይስተዋላል፡፡ ከዚህም የተነሳ የስራ ድግግሞሽ አብዛኛውን ጊዜ ይታያል፡፡ ስራ ለመጀመር የሚያስችል ገንዘብ ኖሯቸው ምን መስራት እንዳለባቸው ግራ ገብቷቸው የተቀመጡም ጥቂት አይደሉም፡፡ እናም "ስራ ለመጀመር የሚያስችል ይህን ያህል ገንዘብ አለኝ፤ ነገር ግን ምን መስራት እንዳለብኝ አላውቅም" በማለት ይጨነቃሉ፡፡ ዕውቀትና የሙያ ክህሎት ኖሯቸው ደግሞ ከቅጥር ስራ ውጪ ሌላ ምንም መስራት የማይችሉ አድርገው ራሳቸውን የሚያስቡ ጥቂት አይደሉም፡፡ ከጅምሩ ስራ ካላገኙ ወይም ከስራ ከለቀቁ የቅጥር ስራን በማፈላለግ ብዙ ጊዜን ሊያባክኑ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በስራ ላይ ያለ ሰው ባለው ትርፍ ጊዜ በመጠቀም ተጨማሪ ገቢ ማግኘት የማይፈልግ አይኖርም፡፡

ስለሆነም እየተሰሩ ያሉትንና አዳዲስ የስራ ዝርዝሮችን መመልከት "ለካ ይህንንም መስራት እችላለሁ" ወይም "ይህ

ስራ ለእኔ ይሆነኛል" ወደሚል እሳቤ ብሎም ትግበራ ይመራል።

ይህ ከ 1000 በላይ የሥራ ዝርዝር የያዘ መጸሐፍ በአነስተኛ ካፒታል፣ በመካከለኛ ካፒታል ወይም በከፍተኛ ካፒታል እንዲሁም ባለሞት ሞያ ወይም ክህሎት በመጠቀም ከቤት ሆነው፣ በበየነ መረብ፣ ሱቅ በመክፈት፣ ቤት ለቤት፣ ድርጅት በመክፈት፣ ፋብሪካ በማቋቋም፣ እጅዎት ላይ ያለውን ገንዘብ፣ ዕቃ ወይም ንብረት፣ የሙያ ችሎታ ወይም ዕውቀት በመጠቀም ምን መስራት እንደሚችሉ ያስተውሉ ዘንድ ሰፊ ምርጫን ያቀረበ ነው። ለተማሪዎች፣ ለቤት እመቤቶች፣ ጥሮታ ለወጡ እንዲሁም በስራ ላይ ላሉ በትርፍ ጊዜዎች በመጠቀም ተጨማሪ ገቢ ሊያገኙ የሚችሉባቸውን ስራዎች እንዲያዩ የሚረዳ ከመሆኑም ባሻገር ለስኬት የሚጠቅሙ መሰረታዊ የንግድ ምክሮችን ያካተተ ነው።

በዚህ መጸሐፍ በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች እንዲሁም በውጪ አገራት አነስተኛና ጥቃቅን ከምንላቸው ስራዎች ጀምሮ ያሉ የስራ ዓይነቶች በክፊል የተዘረዘሩ ሲሆን በተለይ በአነስተኛና በመካከለኛ ካፒታል ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎች ከአዳዲስ የስራ ዝርዝሮች ጋር ተካተዋል። ከአንዳንዱ ሥራ ውስጥ የተለያዩ የሥራ አይነቶችን ዘርዝሮ ማውጣትና አንዱን ብቻ መስራት ወይም በጥቅሉ መስራት የሚቻል ሲሆን ከተዘረዘሩት ስራዎች ውስጥ አብረው የሚሄዱትንም በአንድነት መስራት ይቻላል።

የስራ ዝርዝሮቹን በዚህ መልክ ማቅረብ የተሻለ ነው በሚል በየዘርፉ ተዘርዝረው አልተቀመጡም።

ስለዚህም ይህ መጽሐፍ ብዙ የሥራ አማራጮች እንዳሉ የሚያመላክት ብሎም የሚያማክር ነው። የስራ ዝርዝሮችን በማየት ከፍላጎትዎ፣ ከሙያዎ፣ ከትምህርትዎ፣ ከልምድዎ፣ ከሚሰሩበት አካባቢ፣ ካለዎት መነሻ ካፒታል እና ካለዎት ጊዜ ጋር የሚሄድ መሆኑን በማየትና አዋጪነቱን በማጥናት የሚፈልጉትን ሥራ መጀመር እንዲችሉ ይረዳዎ ዘንድ ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብና የራሴን ልምድ በማከል ያቀረብኩት ሲሆን ህይወትን የሚለውጥ ጥቅም እንደሚገኝበት ሙሉ እምነቴ ነው። በተጨማሪም ሰፊ የሆነ የንግድ ዕውቀት ሊያዳብሩ የሚችሉባቸው የቢዝነስ መጻሐፍት ጥቆማዎች ተካተዋል።

ምንም እንኳ በዚህ መጽሐፍ ብዙ የስራ ዝርዝሮች ቢካተቱም ያልተጻፉም ይኖራሉ። ለምሳሌ በዙሪያችን ያለ እያንዳንዱ መገልገያ ቁስ የሚመረትበት፣ የምርት ግብዓት የሚቀርብበት፣ የሚከፋፈልበት፣ በችርቻሮ የሚሸጥበት፣ አገልግሎት ላይ ውሎ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሂደቶች ሁሉ ብናካትት እጅግ ብዙ ዝርዝሮችን ማውጣት እንችላለን። እንዲሁም በአገራችን የማይመረቱና ከውጪ የሚገቡ ዕቃዎች ሁሉ በሂደት እዚሁ ሲመረቱ የሚኖረው የምርትና የሽያጭ ሂደት ብዙ ስራንና የስራ ዕድልን የሚፈጥር ይሆናል። በተጨማሪም በዕውቀት፣ በተሰጥዖዎች፣ በፈጠራ ስራዎችና፣

በአዳዲስ የስራ ሀሳቦች በእያንዳንዱ ሰው ሊሰራ የሚችል ስራ ተዘርዝሮ አያልቅም፡፡ ሃሳቦችንና ችሎታን በማውጣት ወደ ሥራ በመቀየር፣ ከራስ አልፎ ለሌሎች ስራ ፈጣሪ መሆን አስፈላጊ ነው፡፡

ሥራ መፍጠር በአዲስ ወይም በተሻለ አስተሳሰብ፣ ምርት ወይም አገልግሎት ለሕይወት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን መፍጠር፣ ኑሮን ማቅለል፣ ሕይወትን የተሻለ ማድረግ ነው፡፡

ስራ ለመፍጠር አካባቢያችንን ማስተዋል በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ በቤታችን፣ በሰፈራችን፣ በአካባቢያችን ብሎም በሃገራችንና በዓለም ላይ ላሉ እንከኖች፣ ጉድለቶች፣ ችግሮች፣ የአሰራር ክፍተቶች፣ መተካት መሻሻል ወይም ማደግ የሚገባቸውን ምርቶች ወይም አገልግሎቶችን ሁሉ በማጤን ችግር ፈቺ የሆኑ መፍትሔዎችን መፈለግና ማቅረብ ነው፡፡

በዚህ መፀሐፍ ለተካተቱት የሥራ ዓይነቶች ዝርዝር መረጃና ገለጻ ከፈለጉ ወይም ደግሞ እርስዎ አዲስ የስራ ሃሳብ ካለዎት በማማከር፣ የገበያ ጥናት በማካሄድ፣ ቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀትና ሥልጠና በመስጠት በንግድዎ ውጤታማ ሆነው ካሰቡት ይደርሱ ዘንድ በንግድ ሥራዎች ዕውቀትና ልምድ ባካበቱ ባለሞያዎች አስፈላጊ የሆኑ ሙያዊ ዕገዛዎችን ሁሉ በማድረግ ከጎንዎ እንደምንሆን ከወዲሁ ልንጠቁምዎ እንወዳለን፡፡

ይምረጡ------›ጥናት ያካሂዱ----›ይጀምሩ----›ከስኬት ይድረሱ!

## ይህን መጽሐፍ ካነበብክ በኋላ፡-

- ምን ስራ መጀመር እንደሚገባህና በምን ውጤታማ እንደምትሆን መለየት ትችላለህ፣
- ያላስተዋልካቸውን ስራዎች እንድታይና እንድትመርጥ ያስችልሃል፣
- ከሰፊው የስራ ምርጫ ስራ መምረጥና ወደ ቀጣይ እንቅስቃሴ መራመድ ትችላለህ፣
- ስራ ለመጀመር ያለውን መሰረታዊ ሂደት ታውቃለህ፣
- ቢዝነስ ፕላን ለማዘጋጀትና የገበያ ጥናት ለማድረግ የሚያስችል ዕውቀትን ታዳብራለህ፣
- ትክክለኛ የንግድ ስም እንዴት መምረጥ እንደምትችል ትረዳለህ፣
- ስለ ንግድ ማስታወቂያ ጠቀሜታ ትገነዘባለህ፣
- እንዴት ደንበኞችን ማስተናገድ፣ ማስደሰትና የላቀ የደንበኛ አገልግሎት መስጠት እንደምትችል ትረዳለህ፣
- የስራ ተፎካካሪዎችህን እንዴት ማሸነፍና የገበያ ብልጫ ማግኘት እንደምትችል ታውቃለህ፣
- ምርትንና አገልግሎትን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ትረዳለህ፣
- በስራና በህይወት የሚገጥሙ መሰናክሎችን እንዴት ማሸነፍ እንደምትችል ታውቃለህ፣
- ጊዜንና ገንዘብን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል መሰረታዊ ዕውቀትን ታገኛለህ፣
- በንግድ ስራህ ስኬታማ እንድትሆን የሚያስችሉ ሰፊ የንግድ ዕውቀትን ልታገኝ የምትችልባቸው የመጻሐፍት አርዕስቶች ታገኛለህ፣
- ስራንና የስራ ተነሳሽነትን ይፈጥራል፣ በስራ ላይ ካለህ ደግሞ ውጤታማና ስኬታማ እንድትሆን ይረዳሃል፡፡

# ሥራ የምንመርጥባቸው መንገዶች

አብዛኛው ሰው የራሱን ስራ የመጀመር ፍላጎትና ህልም አለው፡፡ አዲስ ስራ ለመጀመር ስትሞክር ብዙ በሮች በፊትህ ሊዘጉ ይችላሉ፡፡ ብዙ ሰዎችም ሞራልህን ሊነኩት ወይም ሃሳብህን ዝቅ አርገው ሊያዩ ይችላሉ፡፡ ሃሳብህ ላይወደድልህ ወይም "ስኬታማ አያደርግህም" የሚሉ ንግግሮችንም ትሰማ ይሆናል፡፡ ነገር ግን "ማድረግ እችላለሁ!" በል፡፡ ከሁኔታዎች በላይ ለመራመድና ያሰብከውን ለማሳካት የሚያስችል ቁርጠኝነት ይኑርህ፡፡

ከላይ ያለው እንዳለ ሆኖ አዲስ ስራን ልንጀምር ስንወስን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ማወቅ እንዲሁም ማሟላት የሚገባንን ሁሉ ማሟላት ደግሞ ተገቢ ነው፡፡

ለእኔ የሚሆነኝን ስራ እንዴት መምረጥ እችላለሁ? ምን አይነት ስራ ወይም ድርጅት ብጀምር ይሻላል? ከሚለው በፊት በምን አይነት ስራ ነው ችሎታየን፣ ፍላጎቴንና የገንዘብ አቅሜን ልጠቀምበት የምችለው? የሚለውን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

አብዛኞቻችን አዲስ ስራ ስንጀምር ብዙ ማገናዘብ የሚገቡንን ነገሮች ከግምት ውስጥ አንከትም፡፡ ስራ የመጀመር ጽኑ ፍላጎት ብቻ ነው ወደ ስራ እንድንገባ የሚያደርገን፡፡ ይማሬ

ይህ ከ 1000 በላይ የሥራ ዝርዝር የያዘ መጽሐፍ በአነስተኛ ካፒታል፣ በመካከለኛ ካፒታል ወይም በከፍተኛ ካፒታል እንዲሁም ባለዎት ሞያ ወይም ከሁለት በመጠቀም ከቤት ሆነው፣ በበየነ መረብ፣ ሱቅ በመክፈት፣ ቤት ለቤት፣ ድርጅት በመክፈት፣ ፋብሪካ በማቋቋም፣ እጅዎት ላይ ያለውን ገንዘብ፣ ዕቃ ወይም ንብረት፣ የሙያ ችሎታ ወይም ዕውቀት በመጠቀም ምን መስራት እንደሚችሉ ያስተውሉ ዘንድ ሰፊ ምርጫን ያቀረበ ነው፡፡ ለተማሪዎች፣ ለቤት እመቤቶች፣ ጥሮታ ለወጡ እንዲሁም በስራ ላይ ላሉ በትርፍ ጊዜዎች በመጠቀም ተጨማሪ ገቢ ሊያገኙ የሚችሉባቸውን ስራዎች እንዲያዩ የሚረዳ ከመሆኑም ባሻገር ለስኬት የሚጠቅሙ መሰረታዊ የንግድ ምክሮችን ያካተተ ነው፡፡

**አዲስ ሥራ መጀመር ለሚፈልጉና በሥራ ላይ ላሉ ሁሉ!**

- ✔ ከፍላጎትዎ
- ✔ ከሙያዎ
- ✔ ከትምህርትዎ
- ✔ ከልምድዎ
- ✔ ከሚሰሩበት አካባቢ
- ✔ ካለዎት መነሻ ካፒታል
- ✔ ካለዎት ጊዜ ጋር የሚሆንዎትን አዋጪ ሥራ

**ይምረጡ! ጥናት ያካሂዱ! ይጀምሩ!**

አታሚ፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
+251-111 565 352

ዋጋ 150 ብር